# የአቢይ ኑዛዜ!!!

በአየለ ታደሰ
(August 8, 2023)

## መግቢያ

ገጣሚ አይደለሁም፡፡ አንዳንዴ ግን ሕሊናዬ ሲቆስል ግጥሜን በተለየ መንገድ ማቅረብን እመርጣለሁ፡፡ ይህንን በመርማሪ ጋዜጠኛ ዓይን ተመስሎ የድርጊቱ ባለቤት ግን እንደ አድራጊ ወይም ተራኪ ሆኖ በሚተርክ መልክ አዘጋጅሁት፡፡
ለምሳሌ ኧገሌ “እንዲህ ብሏል” ከማለት ይልቅ እኔ “እንዲህ እላለሁ”፤ “መልዕክቴ” ይህ ነው በሚል የኑዛዜ ንግግር ላይ የተመሰረተ ግለሰባዊ ታሪክ ነው፡፡ በአጭሩ እ.አ.አ. 2012 ካቀረብኩት “የመለስ ኑዛዜ” ከሚለው መጣጥፍ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡
መልካም ምንባብ!!!

---

በመርማሪው ጋዜጠኛ ዓይን

“ጤና ይስጥልኝ” ... አለ መርማሪው ጋዜጠኛው፣
አንገቱን ዝቅ አድርጎ ... ለታዳሚው፤
መርሃ ግብሩን ...ሊያቀርብው፣
ያዘጋጀውን ቃለ መጠይቁን ... ሊለቀው፤

እናማ “ታዳሚዎች” አለ ... አልመች ካልኳችሁ፣
የማወራው ... እውነት ካልመሰላችሁ፣
አትስሙኝ አታንብቡኝ ... እባካችሁ፤

እና ገጠመኙን .... ለማውጋት፣
ስለ “ ነጻ አውጭዎች” .... ርቀት፣
አንድ የገጠር ገበሬ ... የተከበሩ አባት፣
ያዋዩትን ለመጥቀስ ... በተምሳሌነት፤
ለመንደርደሪያ ብሎ ... በማንሳት፣
“አዎ እንዲህ አሉ ... እኚያ አባት፣
ሲገልጹ ... የደረሰባቸውን ብሶት፤

ብታንጋግጥ ... ወደ ሰማይ፣
የምትጓዘውን አውሮፕላን ... ብታይ፤
ድምጷን ... ትሰማለህ፣
ግን ከምድር ሆነህ ... ብትጮህ፣
ከርቀቷ መብዛት ... ከቶ አትሰማህ፤
እናማ ስለዘመኑ ... ባለስልጣናት፣
ድምፃቸውን ከመስማት ... ባሻገር፤
በሬዲዮና በቴሌቪዥን ... ከማደንቆር በቀር፤
ቅን ልቦና ... የጎደላቸው፣
የእርኩሳን መናፍስት አስተማሪዎች ... ናቸው”፤

መርማሪው ጋዜጠኛው ... ጭንቀቱ እንዳያስታውቅበት፤
ጅምሩን ደግሞ... እንዳይቆርጡበት፤
ዝግጅቱን ባለስልጣኑ ... እንዳያሰናክሉበት፤
በፍርሃት ልቡ ስትነርት ... በፍጥነት፤
ጊዜም ... እንደሌለው አስተውሎ፣
ወደ ፍሬ ነገሩ ... ተቻኩሎ፤
ጥርሱን ነክሶ ... በልዩ ፍጥነት፤
ያስተዋውቅ ገባ ... እንዲህ በማለት፤

“ የዛሬው መርሃ ግብር፤
ዋነኛው ... ጥንቅር፤
“ውዱ” ... ጠ/ሚኒስትሪያችን፤
አቢይ አህመድ ነው ... እንግዳችን፤

እናማ ... ከዛሬው እንግዳዬ፣
እንዲህ ነበር .... ውሎዬ፤
ግን ... አንድ ነገር ... አይግረማችሁ፣
ከጅምሩ ... ልተንፍስላችሁ፣
ያልተደረገም ... እንዳይመስላችሁ፤
ገና ለመጠይቁ ግብዣ ... ስጠይቃቸው፣
“ጥያቄህን አዘጋጅተህ” ... እንድትልክ ብለው፤
የማያወላዳ “ መመሪያ” ... ሰጥተው፤
ታዲያ ጠያቂ ሳይኖር መልሱን ... ሲያንበለብሉ፡
እንዳያስቃችሁ ... በውሉ፤”

“ በመጀመሪያ” አለ ... ከመነሻው፤
የጀመርኩትን ጥያቄ .... ሳልጨርሰው፤
እንግዳዬ ከአፌ ... ተቀበለው፤

እንደተራበ ጡት እንደሚፈልግ ... ህፃን፤
እንዴ! ለምን ታየኛለህ ... ዓይን ዓይኔን፡
ብለው አጉረጠረጡ
"ታውቅ የለም ... እንዴ፥
ጋዜጠኞችን ... አለመውደዴ፤

*"ታዲያ" አሉኝ... ጣታችውን እየቀሰሩ*
*ወደኔ እያመላከቱ... እያመናተሩ፤*

"ታዲያ" እናንት .... ጋዜጠኞች፣
የወሬ አስጋሪ ... ቀበኞች፤
"ዘረኛ ፋሽስት" ገነመሌ ... ብትሉኝም፣
ቦዘኔ ለማድረግ ... ለማሳጣት ስራችሁን፤
መውረሴ አይቀርም ... ንብረታችሁን፣
ልንገርህ አስረግጬ ... በርግጥም፤
ማናችሁም ብትሆኑ ከዘሬና ዲናሩ....አትበልጡብኝም፤

አሁን ደግሞ በረጋ መንፈስ
ገና ህፃን ሳለሁ በሰባት ዓመቴ፡
"ንጉሥ ትሆናለህ" አለችኝ ... ወላጅ እናቴ፣
ትንቢቷ ተፈጽሞ ...... ባትበቃም ሳታየኝ፡
ለጥቀውም .... ሌላም ብላ ነበር አሉኝ፤
የ'ሰው እንባ' እንዳይገለኝ፤
እኔ ግን በ"መደመር ህሳቤ" ... ተለክፌ፡
"በበሬ ሆይ" ጨዋታ .... ተንዘፍዝፌ፤
የወላጅ እናቴን ... ቃል ቅርጥፍ አድርጌ በልቼ፡
አንከትክቼ አጣጣምኩት...የ"መደመር ህሳቤ"ን ተግቼ፤

በድንገት ያንን ትልቅ ዓይናቸውን እያጉረጠሩብኝ
እኔም ብሆን ... እንድታውቀው፡
በግልፅ ልንገርህ ... ይህ ቃሌ ነው፤
የ"መለሰን" መንገድ ብለቅ ... ይቆራርጠኝ፣
ይቆማምጠኝ ... ከመሬት ይደባልቀኝ፤
ልዩ ተልዕኮ ... ነው ያለኝ፣
የ"ኦነግ" ... ከፋላቸው ነኝ፤"
ለምን አይገባችሁም? ... ይህ ነው ተልዕኮዬ፣
የዝንተ ዓለም ... መለያዬ፤
ከቶስ ምን ትሻላችህ? ... ከስራዬ የበለጠ ማስረጃ፣
ኧረ! አትጃጃሉ አትሁን ... ገልጃጃ፤

የኔ ዲሞክራሲ "ኢትዮጵያዊነትን" ... ደፍሬ፡
በ"ዘር አሳቢ" ትውልድን ... ፈጥሬ፤
የዘመናት ... ባህልህን፡
ለ"ህግ ታዛዥነትህን" ... ልምድህን፡
ይግባህ እንጂ!... አዋርጄ ለማስቀረት ነው እርቃንህን፤
ኢትዮጵዊነትን ... አፈራርሼ፣
የዘመናት ስነ-ምግባርን ... አልከስክሼ፤
አዲስ የጥላቻ ... የዘርን ግንድን አብቅዬ፣
"ኦነግ"ን ከፍ ለማድረግ ... ነው ተልዕኮዬ፤

የአገሬ ህዝብ የዋህ ነው ... በድለላ ቃላት፡
"አስቀድሜ... ከክብሩ ካወረድኩት፤
"ኢትዮጵያ አትከፋፈልም" ... ካልኩት፡
"ስንሞት ኢትዮጵያዊ' ... ብዬ ከሸነገልኩት፡
"ኦርቶዶክስ አገር ነች" ... ብዬ ልቡን ከሰወርኩት፤
የ"ወታደር ጥንካሬና ብቃቱን" ... ብዬ ከዋሸሁለት፡
ተግባሬን እንዳያይ ... ሰውሬበት፡
በዚያ ላይ "Short memory" ነህ ... እያልኩት፤
ስነ ልቡናውን ... አስቀድሜ ካላሸቁት፡
በውዥንብር ናላውን ... ካዞርኩት፤
ተስፋውን ... አጨልሜበት፡
ለንዋይ እንዲገዛ ... ካሰለጠንኩት፡
ለሴተኛ አዳሪ .... ለሌብነት፡
አቦዝኜ ... ለባርነት ካሳደኩት፤
"የማይራባ ወራዳ የማይግባባ ... ለወደፊት፡
ለኢትዮጵያ ትውልድ ... ያሰብኩላት፤
ይህ ነው ቀጣዩ ... የእኔ የአቢይ ምርት፤

እናማ ይግባህ እንጂ ...አዲስ የጥላቻ ዘርን አብቅዬ፣
"ኦነግ"ን ከፍ ለማድረግ ... ዋናው ተልዕኮዬ፤

*"አበስኩ ገበርኩ" አልኩኝ... በድንገት፡*
*ይጨምር ጀመር... የልቤም አመታት፤*

እርስ በርሱ ... እንዳይነጋገር፡
በቋንቋና በክልሉ ... በመማገር፤
ጥቁር ልብስ ... ማቅ አስለብሼ፡
በስነ ልቡና ... አንድን እምነት ... አውርሼ፤
በስመ ... የብሔር ነፃነት፡
አሸመንሙኜ ... ሳቀርብለት፤
ለእያንዳንዱም ... አንዳንድ ቁንጮ ስሾምለት፡
አይጠረጥረኝም ... መርዜን ስረጭበት፤

"እኛ ከመለስ ና ጣሊያን" የተማርነው፡
እንደ ውርስ ቅርስ ... የወረስነው፤
የአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ... ጨርቃችሁ፡
የመቶ ዓመት ... ታሪካችሁ፤
እና ... እኔም ሰማንያ ጨርቆችን ... አበጅቼ፡
በብሄሮች ልክ .... አባዝቼ፤
በተለያዩ ቀለማትና መልክ ... አዘጋጅቼ፡
የመለያ ጨርቃችሁን ... በሺዎች ተክቼ፤
ስነ ልቡናችሁን ... ሰውሬ፡
አዘቅጠዋለሁ ... አሸዋውሬ፤

*ለመሆኑ “ምን ብታደርግህ ነው”? አልኩኝ… በድንገት፡*
*ይጨምር ጀመር … የልቤም አመታት፤*
*ድው ድው ድው … ጨመረ ፍጥነት፡*
*“ወኔዬ” ጠፍቶ … ተውጬ በስጋት፤*
*ታዲያ መደንገጤ … ገብቷቸው፡*
*ለማስፈራራት … ተመችቷቸው፤*

“ትምክህተኛውን” … ምኒልክ ተከትላችሁ፡
አድዋ ላይ … የመለስ አያቶቻችንን … አጥቅታችሁ፤
ጦርነቱን … ገጥመን አሸነፍን፡
እያላችሁ ለዘመናት … ስታበሳጩን፤
እናማ “አድዋ”ን ጀግንነት ከ"ምንሊክ” ለይቼ፡
የ"ምኒሊክ”ን ስም … በ”አቢይ” … ተክቼ፤

አሁንስ ይብቃችሁ … አለቀላችሁ፡
በኔ ዘመን … ስለ አያቶቻችሁ ብላችሁ፡
ይቅርታ … ጠይቃችሁ፤
አሊያም የአድዋን በዓል …በስሜ ሰይማችሁ፡
በይቅርታ … ካልሰገዳችሁ፡
ከምድር ገፅ ነው … የማጠፋችሁ፤
ይህ ነው የናንተ …. ዋጋችሁ፤

*“መሪያችን” የአድዋ ድል … ካበሳጫቸው፡*
*በርግጥም “ንክ” … ናቸው፤*
*አልኩና በልቤ … እስከመጨረሻው፡*
*ላልተነፍስ … ወሰንኩኝ ላስጨርሳቸው፤*
*አእምሮአቸው የታወረ … ሸውራራ፤*
*የጥላቻና … የብቀላ ጎራ፤*

እናማ ይግባህ እንጂ …አዲስ የጥላቻ ዘርን ኦብቅዬ፣
“ኦነግ”ን ከፍ ለማድረግ … ነው ተልዕኮዬ፤

ታውቅ የለም እንዴ የስነ ልቡናን ጥልቀቴን፡
ሳር ቅጠሉ እንዲወደኝ የማድረግ ችሎታዬን፤
በየዕለቱ “አዳዲስ አጀንዳ” የመፍጠር ብቃቴን፤
“ብልጽግና”ን የፈጠርኩላችሁ፡
ጦርና ብር ታንክ ውሸት … ተሸክሜላችሁ፤

የኦሮሞ ተወላጆች ከጎኔ … እንዲሰለፉ፡
አማራ “የኦሮሞ ጠላት” ነው ብለው …እንዲለፍፉ፤

የዋሁን ወገኔ … ከጎኔ እንዲሆን፡
እርስ በርሱም … እንዳይኳኳን፤
የጥላቻ … የፍርሃት ድባብ፡
የመነጣጠል … እኩይ ጥበብ፤

እናማ በወለጋ ላይ … የሞከርኩት፡
ውጤት …. ስላገኘሁበት፤
አሁን ደግሞ … በአማራና በሌላው ምድር፡
በስፋት … እንዲተገበር፤

አንዱ …. ለአንዱ፡
ሌላው …. ለአንዱ፤
ጉራጌ ለኦሮሞ … አፋሩ ለጋምቤላ፡
ጥላ እንዳይሆናቸው … ከለላ፤
እርስ በርሳቸውን ማበጣበጥ … ነው ዘዴዬ፡
ሁሉንም ከፖለቲካው መስክ … ነጥዬ፤

በሁሉም መስኮች … የኦሮሞ ተወላጆች፡
አዛዥ ፈላጭ ቆራጭ እንዲሆኑ … ሹመኞች፤
ኦሮሞውን ከሌላው …. በማባላላት፡
እርስ በርሱንም … በማሻኮት፤

በሰከነ መንፈስ

አማራውን፤ ጉራጌንም ከንግዱ መስክ መንጥሬያለሁ፡
ንግዱን ፖለቲካውንም … በኦሮሞ አስይዣለሁ፤
የስለላው አውታር … ዘርግቻለሁ፡
የሩቅ ትልሜን …. ነድፌያለሁ፤
ፖለቲካውንና መሬቱን … ለኔ ትታችሁ፡
እድሜ ልካችሁን አንገታችሁን ደፍታችሁ፤
ሀ ሀ ሀን ብቻ … ተሸክማችሁ፤
እንድትኖሩ ነው የምሰራላችሁ፡
በወጥመዴ ስር ወድቃችሁ፤

እንደያውም ዲያስፖራዎች … እዚህ ለጉብኝት ስትመጡ፡
ምድሪቷን ገና … ስትረግጡ፤
የቤትና ንብረት … ባለቤት ሆናችሁ፡
እንደ ዕቃ በብድር … ይዤያችሁ፤
አመጽ ላይ እንዳትሳተፉ … “ቃል” ገብታችሁ፡
ቤተሰባችሁ … እንዲሰልሏችሁ፡
ጓደኞቻችሁ … እንደያጋፍጧችሁ፤
በፓርቲዬ ሰላዮች … ታጅባችሁ፤
የዋላችሁበትን … እንዲያቀርቡ፡
የበላችሁትን … ዝርዝር እንዲመዘግቡ፤
አሊያ ግን … ግዞት ነው የሚጠብቃቸው፡
ወደፊት … ስራም እንጀራም የላቸው፤

የ”መደመር”ን መንገድ ብለቅ … ይቆራርጠኝ፡
ይቆማምጠኝ … ከመሬት ይደባልቀኝ፤
ልዩ ተልዕኮ … ነው ያለኝ፡
የዘራቸውም … ክፉላቸው ነኝ፤”
ለምን አይገባችሁም? … ይህ ነው ተልዕኮዬ፡

የዝንተ ዓለም ... መለያዬ
ከቶስ ምን ትሻላችህ? ... ከስራዬ የበለጠ ማስረጃ
ተከታዮቼ! አትጃጃሉ አትሁን ... ገልጃጃ፤

ባለቤቴ ዝናሽ ... ዘርዋ የጠራ፡
የ"ትምክህተኛው" .... አማራ፤
የኔን ተልዕኮ ... የተሸከመች፡
ንዋይ የምትርጭ ... ለገንዘብ የሞተች፤
እጇን በሁሉም መስክ ... ለባሏ የሰጠች
ለ'አማራ" ህዝቦች ... የጥፋቴ አላማ፡
ዋና መሰላል ... ስኬታማ፤
ለዚህ ልዩ ተልዕኮ ... የተሸከመች፡
ባለቤቴ ... እስዋ ብቻ ነች፤

*የአማራ ጥላቻ ... ካለባቸው፡*
*ለምንድነው አዜብን ... ማግባታቸው፤*
*አልኩና ላንዳፍታ፡*
*ይዞኝ ሲሄድ የሃሳብ ሽውታ፤*
*ከራሴም ጋር .... ስሟገት፡*
*ንግግራቸውን ቀጠሉ እንዲህ በማለት፤*

"ታውቅ የለም ... እንዴ፡
ጋዜጠኛን ... አለመውደዴ፤'

*አሉ ድምፃቸውን ከፍና ዝቅ አድርገው፡*
*አፍረት በማያውቀው ... አንደበታቸው፤*

እኔም ብሆን ... እንድታውቀው፡
በግልፅ ልንገርህ ... ይህ ቃሌ ነው፤
የ"መደመር"ን መንገድ ብለቅ ... ይቆራርጠኝ፡
ይቆማምጠኝ ... ከመሬት ይደባልቀኝ፤
ልዩ ተልዕኮ ... ነው ያለኝ፡
የ"ኦነግ" ርዕዮተ ዓለም ... ከፋላቸው ነኝ፤"
ለምን አይገባችሁም? ... ይህ ነው ተልዕኮዬ፡
የዝንተ ዓለም ... መለያዬ፤
ከቶስ ምን ትሻላችህ? ... ከስራዬ የበለጠ ማስረጃ፡
ተከታዮቼ፡ አትጃጃሉ አትሁን ... ገልጃጃ፤
*ታዲያ አሉኝ ... የቀኝ ጣታቸውን እየቀሰሩ፡*
*ወደኔ እያመላከቱ ... እየሰገሩ፤*

የገንዘብ ምንጫችን ... ፈረንጆቹ፡
ልብ የሌላቸው ... "እቃዎቹ"፤
ሲ.አይ.ኤ. ... እና ሌሎች ሰላዮቻቸው፡
ያሉኝን ... ከፈፀምኩላቸው፡
ለሌላው ነገር ... ቁብም የላቸው፤

ስለዚህ ... የምግብ እህሎችን፡
ጥራጥሬ ... ፍራፍሬዎችን፤
ሁሉንም የግብርና .... ምርቶችን፤
በዘዴ ... በእጥረት እያሳበብኩ፡
ገንዘብ ሳተርፍ፡ ... በዶላር እየመነዘርኩ፤
የዛፍ ተክል ... ለሬሳ ጥላ ይሆናል፡
ትንግርት ብጤ ፈጥሬ .... ገንዘብ ለመቀበል፤
እንዲሁም የኮሬንቲውን ... ውጤት፡
እናንተ ሳታዩት ... ሳትጠቀሙበት፤
መስመሩን ወደ ውጪ በመዘርጋት
መቸብቸብ ነው .... ለጎረቤት አገራት፤

ሁለቱን ገፅታ ... አንግቼ፡
"ውርደት"ን ለናንተ ... "ክብር"ን ለአለቆቼ፤
ሥረ መሰረታችሁን አናግቼ፡
የማንነታችሁን ፋና ... አጥፍቼ፡
ቅርሳችሁን ... አደባይቼ፤
አሳርሬና አድብኜ .... ቆሽታችሁ፤
ስኳሩ ልብ ድካሙ ... እንዲሆን ዋጋችሁ፡
ባለ በሌለ ... በሽታ ታሽታችሁ፡
አመርቅዞ ... እንዲገላችሁ፤
እናማ የዋዛ ... እንዳልመስላችሁ፡
ይህንን ነው ... ለናንተ የምሰራላችሁ፤

*ግሩም ኑዛዜ .... ነው፡*
*የ"መሪያችን" ... የጣሊያን" ባንዳ" ው፤*
*ዓላማው ... ባይገባኝም፡*
*ታሪኩም ... እጅ እጅ ቢለም፤*
*ከራሴም ጋር .... ስሟገት፡*
*ንግግራቸውን ቀጠሉ ... እንዲህ በማለት፤*

በረሃብ አለንጋ ... ጠውልጋችሁ
በቸነፈር ... ተገርፋችሁ፤
የደረቀ እንጨት ... አክላችሁ፡
በበሽታ ተባዮች ... ተከባችሁ፤
ድርቅ ሆኖ ... መለያችሁ፤
የዓለም መሳለቂያ እንደ ሆናችሁ፡
አሁን ደግሞ ... በውሸት ትርክት፡
ከ"ኦሮሞ" ውጭ የሆናችሁ ... እንድትኖሩ በባርነት፤
አሊያ ግን የስደት ዓርማ ... አንግባችሁ፡
በባህርና በየብስ ... ስትኮበልሉ ጥላችሁ፤
የተሳካላችሁ ... ደርሳችሁ፡
ያልተሳካላችሁ ... ባህር በልቷችሁ፤
"አገር እንደሌላቸው" ... እንደ ጂብሲዎች፡
ስትንከራተቱ ... ባይተዋር ሆናችሁ፤
ከምድረ ገፅ .... ስትጠፉ ማየት፤

ነው የደስታዬ ወሰን … ስሜት፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ … ደስታ ይኖረኝ ነበር፤
….. ተፈጥሮንም … ብቆጣጠር፤
ፀሐይዋንም ብጋርድ … ብርሃኗን ብከልል፤
ከጭለማ እንዳትወጡ … ለዘላለም ማድረግ ብችል፤

*ከቶ ማመን አቃተኝ፤*
*ውስጤ ደም ሲፈላ ተሰማኝ፤*
*ምሬታዊ … የእብሪት አነጋገራቸው፤*
*ከቶ ኢትዮጵያ ምን ብታደርጋቸው ነው?*
*አእምሮአቸው የታወረ … ሸውራራ፤*
*የጥላቻ … የብቀላ ጎራ፤*
*ኢያልኩ ከራሴ ጋር ስሚገት፤*
*ንግግራቸውን ቀጠሉ እንዲህ በማለት*

የኦክሲጅኑም አየር … እግዜር በነፃ የሰጣችሁ፤
እሸጥላችሁ ነበር … በገንዘባችሁ፤
ለ"ጫካው ፕሮጀክት" መሥሪያ፡
እናንተን ከቀያችሁ …ማፈናቀያ፤
ማይዘለፋ ደባልቄበት … እንዲያሳብዳችሁ፤
ከምድር ጠራርጎ …. እንዲያጠፋችሁ፤

*እንዴ ምንድነው የያዛቸው፡*
*ልክፍት ነው የሚያናግራቸው፤*
*ምናልባት ከአዶከበሬ … መልስ፡*
*ጨብሲ ለማለት ተጎንጭተው እንደሆነስ፤*
*ቀስ ብዬ የአፋቸውን የጠረን ሽታ፡*
*ሳሸት በእርጋታና …. በቀስታ፤*
*አጀብ ነው! … ከቶውንም አልቀመሱም፡*
*ማስቲካም ቢሆን … አያላምጡም፤*
*ታዲያ የኢትዮጵያ ጥላቻ ካለባቸው፡*
*ፀሐይዋን ለመጋረድ አየር ለመሸጥ ካስመኛቸው፡*
*በርግጥም እብሪት ነው ያለባቸው፡*
*ያለቀለት ልክፍት ነው … በሽታቸው፤*

*በድጋሚ … ጣታቸውን እየቀሰሩ*
*ወደኔ እያመላከቱ … እየሰገሩ፤*

የ"አገር ፍቅር" ስሜት በሌላቸው … አሽቃባጮች፡
የዘመኑን የእምነት … ጉዶች፤
በሃይማኖት ፅንፈተኞች … ሞልቼ፤
መሬታችሁንም ለባዕዳን … ከፍቼ፤
እኔም የድርሻዬ … ዲናሬን ሸምቼ፤
ዘላለማዊ የፀብ ዘርን … ዘርቼ፤
የምትመኩባትን "ኢትዮጵያ" … ከካርታ አጥፍቼ፤

እናንተ ግን … ሁለተኛ ዜጋ ሆናችሁ፡
በገዛ አገራችሁ … ቀዬ… መንደራችሁ፡
እንዳንትሰራሩ ነው … መቃብር የቆፈርኩላችሁ፤

ሥልጣኔን ለማራዘም … ለማስጠበቅ፡
አጀንዳ በማብዛት … ጦሬን በመስብቅ፤
ፋኖ ሲመጣብኝ … 'እኔም ፋኖ ነኝ ብዬ"፡
አወናብዳለሁ … አፍዝ አደንግዙን ቀጣጥዬ፤

*ይህች ናት ማጭበርበር!*
*ብዬ አፌን ሳላውስ !*

መቼም በአገሩ ጉዳይ … ስመጣበት፡
"ፍላጎቱ"ን … እንደማውቅለት፤
አይጠራጠረኝም ይሰጠኛል … ጥንካሬ ጉልበት፡
በስነ-ልቡናው …. ስጫወትወበት፤
ስሜቱን … እርስ በርስ በማጋጨት፡
ወንድነቱን … ሳኮላሸበት፤

በረሃብ ገርፌ እያማረርኳችሁ፡
አዲስ አበባን … ከዙሪያዋ ገንጥዬላችሁ፤
"ሸገር"ን ከተማን … በማልማት፡
ኃይማኖታዊ ባህልን … ተውፊትን በማጥፋት፤

የተፈጥሮ ጉልበት … በማኮስመን፡
ደኖችን ዛፎችን …. ማመንመን፤
ለም መሬታችሁ … እንዳታፈራ፡
ዘር እንዳታወጣ … እንድትሆን መራራ፤
ማድረግ ነው … የማዳበሪያ እከክ፡
የምግብ ሳይሆን … የኬሚካል አበባ መስክ፤
ብሄሮችን በማጋጨት… እሳት በመለኮስ፡
በማተናኮስ ማላተም … እርስ በርስ፤

እናማ ልንገርህ በውነቱ፡
የ"ኢትዮጵያዊነት" ስሜት … ውጤቱ፤
አመርቅዞ እንዲጠዘጥዛችሁ፡
በቁማችሁ እንዲገላችሁ፤
ገምጂ ነው የምተውላችሁ፡
ለዘላለም ሰላም እንዳይኖራችሁ፤
ሥጋችሁ ስበላ … ይጥመኛል፡
ደማችሁ … ጥሜን ያረካኛል፤
ስቃያችሁ … ያስደስተኛል፡
ሰቆቃችሁ ዋይታችሁ… ያስቦርቀኛል፤
መከፋፈላችሁ … ስልጣኔን ያረዝምልኛል፤

*እንዴ አሁንስ አበዙት!*

የዘመናችሁ ትውልድ … በእጄ ያለው፡
የአድዋ የማይጨው … ጊዜ የከዳው፤

---------------------------------------------------------------------------////////////////////////////////---------------------------------------------------------------------------

የ“ጀግና” ልጅ … ነፍላላው፡
አያሸወረርኩ … እየው ገደል ስከተው፤
የማትፈለጉትን ማሰር … ማንገላታት፡
በኋላም ይቅርታ አስጠይቆ … መፍታት፤
ደግሞ “ኃላፊነት” ብሎም… የአገር ፍቅር፡
የተጠናወታችሁ … ተልካሻ ነገር፤
ዲናር አይሆን … ሆድ አይሞላ፡
ያስቀራችኋል …. የባሰውኑ ወደ ኋላ፤

ተረዱልኝ እወቁት … ነው የምላችሁ፡
የዘሬን ብለቅ ይቆማምጠኝ ብያለሁ፤
ከዚህ በላይ አስረጂ ካሻችሁ፡
በአራቱ ማዕዘን ፍሬዬን አይታችሁ፤
በጦርነት ታጥራችሁ፡
ሰላምን አሳጥቼያችሁ፤

በይሉኝታ … ተይዛችሁ፡
በባህል ተፅዕኖ ስር … ሆናችሁ፤
በሽምግልና … አባዜ ተይዛችሁ፡
እኔን ወደ ልቡ … ይመለሳል ብላችሁ፡
እንዲያው ነው … መድከማችሁ፤

ጊዜ እንስጠው … አይጨክንም፡
ብትሉም በሰላም እንታገል … ለሁሉም፤
እናማ ቀልድ … አላውቅም፡
ከቶውኑ … ለምን አይገባችሁም?
ለዚህ ሁሉ … ልፋታችሁ፡
እንጦርጦስ … እንደሚጠብቃችሁ፤

እኔ … የምፈልገው፡
መስማት ማየት … የምመኘው፤
የባዶ ቃላት … ቻቻቻ፡
ጉንጭ አልፋ … ስልቻ፤
ማጋጨት … ማተራመስ፡
በከንቱ ውዳሴ … መወደስ፤
የወታደሮቼ ጠብ መንጃ … እምነቴ፡
የሰላዮቼ መጥለፊያ … ህይወቴ፤

ስለ ኃላፊነት … ከምታወሩ፡
ሁሌ … ከምትቀበጣጥሩ፤
ከኔ ጎራ ተሰልፋችሁ … አሰልፋችሁ፡
ስለዲናር ብላችሁ … አግዙኝ ነው የምላችሁ፤

“ታውቅ የለም … እንዴ፡
ጋዜጠኛን … አለመውደዴ፤

በቴረሪዝም … ወንጀለኝነት፡
አጥፍቶ ጠፊ ስም … ቅጣት፤
እንድገለብጣችሁ … የወፌ፡
በህገ መንግስት … አስደግፌ፤

ድሃውን አሰቃይቼ … በእርዛት፡
በስመ የዛፍ ተከላ የአገር … ልማት፤
በጦር መሳሪያ … ተማዛችሁ፡
እንደ ሶማሊያ … ተበታትናችሁ፤
እስከ … ልጅ ልጆቻችሁ፤
እንዲወርሱት …. መለያየታችሁ፡
እንዲገፉት … የአንድነት ኃይላችሁ፤
ለኦሮሞ ህዝብ የቆምኩ … መስዬ፡
የአማራ ጭራቅ … መጣብህ ብዬ፤
እኔም እንደ … “መለስ”፡
ሥራውን … በመውረስ፤
ዘራቸውንና አንድነታቸውን … ለማክሰም፡
ትውልድ ቀዬያቸውን … ለማዳከም፤
የ“አማራን” … ሴቶች፡
ምንም ያላወቁ … ህፃናቶች፤
ለግርድና … ወደ አረብ አገር፡
ለማግኘት ወፈር ያለ … ዲናር፤

*በድጋሚ … ጣታችውን እየቀሰሩ*
*ወደኔ እያመላከቱ … እየሰገሩ፤*

በተረፈ ጋዜጠኛ … ብሎ ነገር፡
… ወደ እስር ቤት መወርወር፤
እውነቱን ለመሸፈን … ለማሸፈት፡
የ”በሬ ወለደ” … ውሸትን ማሰራጨት፤

አገሩን ምድሩን ለማተራመስ … ለማሳረር፡
ሐሰቱ … አውጥቶ እግር፤
እውነቱ … አጥሮ ሲተጣጠፍ፡
በውሸት ተከልሶ … ሲከንፍ፤
በውዥንብር … ዓለምን ሳደናግር፡
“አዋቂ” እንኳ … ለማመን እስከሚቸገር፤

ቤተሰባዊ … አንድነታችሁ፡
በሰላዮች … መርገፃችሁ፡
መተማመን … እንዲያቅታችሁ፤
ፍቅራችሁ አመርቅዞ … እንዲገድላችሁ፡
በቁማችሁ … የሞት ሞትን ተሸከማችሁ፡
አሳብዶ … ጨርቅ እንደያስጥላችሁ፡
በየሄዳችሁበት እንድታወሩ … ለብቻችሁ፤
ሰልቤ… ስነ ልቦናችሁን፡
ይሉኝታና … የአክብሮት ገበናችሁን፤

---------------------------------------------------------------------------///////////////////////////////----------------------------------------------------------------------------

የእናንተነትን .... መሰረት፡
የአንድነታችሁን ... ሰንሰለት፤
ታሪክ ቅርሳችሁን ... አርክሼ፡
"ኢትዮጵያዊነታችሁን" ... ደምስሼ፤

የዘርማንዘሬን ብለቅ ... ይቆራርጠኝ፡
ይቆማምጠኝ ... ከመሬት ይደባልቀኝ፤
ልዩ ተልዕኮ ... ነው ያለኝ፡
የዘራቸውም ... ከፋላቸው ነኝ፤"
ለምን አይገባችሁም? ... ይህ ነው ተልዕኮዬ፡
የዝንተ ዓለም ... መለያዬ፤
ከቶስ ምን ትሻላችህ? ... ከስራዬ የበለጠ ማስረጃ፡
አትጃጃሉ አትሁን ... ገልጃጃ፤

*የወደፊቱ ዓላማቸው ሲያወሱ*

"ከፉ ድርጊት"ን ሁሉ ... "አለማምጄ"፡
አስገብቼያችሁ በመዳፌ ... በእጄ፤
አነጋዊ ኃላፊነቴን ተወጥቼ .... ፡
ቃሌን እንደምታምኑ ... ገምቼ፡
ካላመናችሁ ደግሞ ... ፀብን ዘርቼ፤
ምናልባትም... እኔ ያልጨረስኩትን፡
ጀምሬ የተውኩትን... ያልጨረስኩትን፤
እንዲቀጥል ትውልድ ተክቼ፡
የታላቋ ኦሮሚያ ... ህልሜን ይተገብሩታል ልጆቼ፡
ይተገብሩታል ጓዶቼ፤

እንደ እኔ ... "የባንዳን" ስም ተሸከመው፡
ሌት ተቀን የቆሙ ... ለሰላቶው፤
አሊያም ... የዋህ መሰሎችን፤
ፍርፋሪ ለቃሚ ... ጀሌዎችን፡
ከጀርባዬ ያለውን ... የማይጠይቁትን፤
እኔኑ ለመጥቀም ... ስትራወጡ፡
የምትሰሩትን ሳታገናዝቡ ... በቅጡ፤
እንደ ሸንኮራ ልጣጭ... መጥጬ፡
ሲበቃኝ ... በሙስና አዝቅጬ፤
ወደ እስር መጣል ነው... መቀመቅ፡
መንገዱን ለተረኛው ደግሞ... እንዲለቅ፤
ሙያን ከሙያተኛ .... ለማራራቅ፡
በግምገማ ሞራላቸውን ... ማዳሸቅ፤
መምህር የሆኑ... ከጠየቁ መብታቸው፡
ከስራ ማባረር ነው .... መፍትሄው፤

ሙግታቸውን ... ለማስከን፡
በምትካቸው ... ውዶቹን፤
ውሃ ቀጠነ ... የማይሉትን፡
ስለሙብት የማይጨነቁትን፤

የውጪ ዜጎች ... ውጭ የሰለጠኑትን፤
እንደ ሸቀጥ ... ከውጭ አገር፡
አስመጣለሁ ... በዶላር፤

እርስ በርስ መተማመን ... ማክሰም፡
ማጥፋት... እስከ ወዲያኛው ዓለም፤
ንግድና ... የምጣኔ ሃብት፡
ትምህርትና ... ንብረት፤
የኦሮሞ "ወዳጆቼ" ... እንዲበሸበሹበት፡
የስልጣን እርከን ... እንዲይዙበት፤
ዘጠና ዘጠኙ ... እንዲጠፉበት፡
የኔብጤ ጥቁር ... ሽሚዝ ለባሾች
በንዋይ የተገዙ ... ቅጥረኞች

አትፈለጉም በተመለከተ

እናንት አትፈለጉም ... ውጡልኝ ከምድሪቱ፡
ታሪካችሁንም አልሻም ... አትሁኑ ገልቱ፡
አሊያም የምሰራውን አርፋችሁ ተመልከቱ፤
እያያችሁ ላታዩ... የሌላው የስቃይ ገመድ፡
ተጃጅላችሁ... በ"ገለልተኛ" ወጥመድ፤
ጣልቃ ላትገቡ ... ስትማማሉ፡
ወረፋችሁ እስከሚደርስ ... ከመንገዱ ገለል ልትሉ፤
ስደት ግቡ ... ከውቅያኖስ ባሻገር፡
ድምፃችሁን ... ከማልሰማበት አገር፤
እንጦርጦስ ግቡ ... የአውሬ ራት ሆናችሁ፡
በዓለም ዙሪያ ... በዝቶ ስቃያችሁ፤

ባህል ታሪክን በተመለከተ

የስነ ልቦናችሁን ሰልቤ
የአክብሮት ትሁትነታችሁን ... አጥፍቼ፤
ባህላችሁን ... ከላልሼ፡
ኢትዮጵያዊነታችሁን ... አርክሼ፤
ማየት ነው ... የምመኝላችሁ፡
አወዳደቃችሁን ... እንዲያሳምርላችሁ፤
የምንጫችሁ የእምነት ... ባህል፡
'ኢትዮጵያ' የምትለዋን ቃል፡
የአይሁድ ምልክት እምነታችሁን ለማጥፋት፡
ከመፅሐፍ ቅዱስ ... በማውጣት፡
የእናንተናችሁን ምንጭ ... መሠረት፤
ገዳማት ሆኑ ... አድባራት፡
የታሪክ ቅርሳችሁን አብሮ ማጥፋት፤
እስከ ወዲያኛው ... ማናጋት

የታሪካችሁን መሰረት ከላልሼ፡
ለመጪው ትውልድ ... መከፋፈልን አውርሼ፤
የውጪውን የእግር ኳስ ... ጨዋታ፡
የህዝቡ ... የልብ ትርታ፡
ለኔ ግን ትልቅ ... እርካታ፡

---

ለስልጣን ማቆያ ... እፎይታ፤

ቅንድቡ ያምራል ... ቢሉኝ፡
በሽሙጥ ... ቢዘፍኑልኝ፤
እኔ እንደሁ ... እኔ ነኝ፡
ይቅርታ የሚሉት ነገር ... የማይገባኝ፤

*በድጋሚ ... ጣታችውን እየቀሰሩ*
*ወደኔ እያመላከቱ ... እየሰገሩ፤*
መንገዴን ... ተረዳልኝ፡
እንጂ ... አትለምነኝ፤
መንገዴን ለማፅዳት ብዬ፡
ብዙ ቤተሰብ ... ብሏል ይላል እዬዬ፤
ስደተኛ ሁኑ ... በምርጫችሁ፡
ሁለተኛ ዜጋ ... ሆናችሁ፡
ዓለም የሲያል ምድር ... እንድትሆንባችሁ፤
የህሊና ስቃይ ... ገፈታ፡
ራስን የመጥላት ... በሽታ፤
የጉበት ስኳር ... ጨጓራ፡
የልብ ህመም ... የአእምሮ መራራ፤

እሳት በመለኮስ ... ህዝቡን በማጋጨት፡
የጋራ የኑሮ ባህልን ... ማጥፋት፤
አሊያም በዘዴ ... ማሰቃየት፡
የኑሮ ጉሮሮአቸውን ... በመዝጋት፤
ማየት ነው ,.. የምመኘው፡
ለሁሌም ... የምደክመው፡
ደፋ ቀናም ... የምለው፤
እንደ ሶማሊያ ... ተበታትናችሁ፡
ለልጅ ልጆቻችሁ ... አገር እንዳይኖራችሁ፤

እኔን ለማውረድ ካሻችሁ፡
በጠብ መንጃ ካላመናችሁ፡
በሰላማዊነት ካመናችሁ፤
እውነቱን ልንገራችሁ፤
"ሰላማችሁ" ... ያስፈራኛል፡
ህብረታችሁ ያሸብረኛል፤
የዘመኑ "ፋኖ" ... እንቅልፍ ነስቶኛል፤
በህቡዕ ... ስትደራጁ... ያስፈራኛል፤
እናማ እስከ "ህይወቴ" መጨረሻ፡
እፋለማለሁ እስከ እስከመዳረሻ፤

*ተመልካቾቻችን ለዛሬ ያለኝ ዝግጅት*
*ከማጠቃለሌ በፊት*
*ልብ ያለው ... ልብ ይበል፡*
*ጉንዳኑ ተዋጊ ይመስላል፡*
*ግን ፍርሃቱ ... አይጣል፤*
*በሰላዮቹ በሠራዊቱ ... የሚመካ ነው፡*
*ቅንጣትም "ጀግንነት" ... የሌለው፤*

*እናማ ጉዞው ረጅም መንገድ ... አቀበት፡*
*የበዛበት ተዳፋት... ቁልቁለት፤*
*የሚያስከፍል ... ብዙ መስዋዕት፤*
*በከተማ ያላችሁ ... አዲስ አበባዎች፡*
*የዚህ ዝግጅት ታዳሚዎች፤*
*አታቃጥሉት ... ራሳችሁ፡*
*አትሰቀሉ ... በየጓዳችሁ፤*
*ይልቅስ ወደ አደባባይ ውጡ፡*
*ውጤት እንዲኖረው ... ለውጡ፤*
*ቀጠሮ ይዛችሁ ... በአንድነት፡*
*ትመሙ ... ወደ ምኒሊክ ቤት፤*
*ምናልባትም ብትሰዉ ... ይፃፋል ስማችሁ፡*
*ይወሳል ይወደሳል ... ታሪካችሁ፤*
*ሐውልት ... በየከተማው ቆምላችሁ፡*
*ለዘላለም እንደ "ፋኖ"... ትዘከራላችሁ፤*
*ትባላላችሁ ... የችግር ጊዜ ደራሾች፡*
*የ"ነፃ አውጪ ግንባር" ... ቀባሪዎች፡*
*የኢትዮጵያ ውድ ... የሰማዕት ልጆች፤*

--------- **ተፈፀመ** --------

አስተያየት ካሎት በ ayele615@gmail.com ያገኙኛል፡፡